# አገራዊ የፖለቲካ አደረጃጀት ለኢትዮጵያ ብቸኛው አማራጭ ነው

## ጎሰኝነት ትልቅ አገር አይገነባም

ከፍቅረስላሴ ወርቅነህ

## <u>መግቢያ</u>

ይህ ጽሁፍ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅትን አመጣጥና ከዚያም በኋላ ያለውን ሁኔታ የሚዳስስ ቢሆንም ለሰፊው አንባቢ ግንዛቤ ለመፍጠር የታለመ እንጂ የምርምር ጽሁፍ አይደለም። ብዙዎች ክስተቶች ከአንድ ትውልድ በላይ የማይርቁ በመሆናቸው ዋቢ እያጣቀሱ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም። የጽሁፉ ዋና ዓላማ በጎሳና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አደረጃጀት ውሎ አድሮ አገር ሊያፈርስ እንደሚችል በማሳየት አሁን ባለንበት የሽሽግግር ወቅት አደጋውን አገናዝበን አገራዊ ወደ ሆነ አደረጃጀት ጊዜው ሳይረፍድ ትኩረታችንን እንድናቃና ለመማጸን ነው። ከዚያም ባሻገር በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው ዝምታ ተሰብሮ ህብረተ ሰቡ በስፋት እንዲወያይበትና የተደራጁ ቡድኖች ላይ ጫና እንዲፈጥር ለመገፋፋት ነው። ምስጋና ይግባቸውና ዶክተር አቢይ መሰነጣጠ የሚያስከተለውን ጉዳት በማመላከት ፖለቲከኞች እንዲሰባሰቡ ጥሪ ሲያቀርቡ ቆይተዋል፤ ያ ጥሪ በአገር አቀፍ ደረጃ የተደራጁ ፓርቲዎች መካከል ትንንሽ የመሰባሰብ እንቅስቃሴዎች እንዲጀመሩ ረድቷል። እኛ ደግሞ እርሳቸው ፖለቲከኛ በመሆናቸው ሊያነሷቸው የፈሯአቸውን ጥያቄዎች እያነሳን ወደ ውይይት መድረክ ማቅረብ አለብን። የእከሌና የእከሌ ነጻ አውጪ ግንባር ተብለው የሚንቀሳቀሱ በርከታ ድርጅቶች ባሉበት አገር ምን ያህል በጎ አመለካከት ቢኖረን፤ ጊዜያዊ መፍትሄ እንጂ ዘለቄታ ያለው ጠንካራ አገር ልንገነባ አንችልም፤ እንዲያም ሲል አንድ ቀን አንዱ ሲያኮርፍ፣ ያቺ ከስሙ ጋር ተቆራኝታ የተቀመጠችው የነጻነት ጥያቄ የምትመዘዝ ይመስለኛል።

ስለዚህም ትልቁን ጥያቄ የማቀርበው በቋንቋ ዙሪያ ለተደራጁ ግንባሮች ነው፤ ጥያቄውም ቀጥተኛ ነው፤ የጎሳ ድርጅት እንድናቋቁም ያነሳሱንን የሙብትና የእኩልነት ጥያቄዎች ቢኖሩም፣ ጥያቄው በአንድ ዘመን የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው ተብሎ ቢራገብም፣ አሁን ላይ ግን ጥያቄው ጊዜ ያለፈበት፣ የቆረፈደ እንደሆነ እናስተውላለን። በመሆኑም አሁን ማድረግ ያለብን በጎሳ ስም የተደራጁ ሁሉ ወደ ሚስማማቸው አገራዊ ፓርቲ እንዲቀላቀሉ መጋበዝ ነው፣ ወይም አዳዲስ አገራዊ ይዘት ያላቸው ፓርቲዎች ፈጥረው ሌሎችን በዙሪያቸው እንዲያሰባስቡ ማድረግ ነው። ይህ ሂደት ደግሞ ከገዢው ግንባር ቢጀምር ትልቅ አርአያነት ይኖረዋል ብዬ እስባለሁ። ያ ማለትኢሕአደግን ለማቋቋም የተሰባሰቡትን የብሄረሰብ ድርጅቶች አፍርሶ ወደ አንድ በዜግነት ላይ የተመሰረተ አገራዊ ፓርቲ መጠቃለል ማለት ነው።

ከዚህ ቀጥሎ፣ የፖለቲካ አደረጃጀት በአገራችን በየዘመኑ ምን እንደሚመስል ለማሳየት እሞክራለሁ፡-

1) በንጉሳዊ አገዛዝ ዘመን ፖለቲካና የፓለቲከኞች ሁኔታ ምን ይመስል ነበር
2) በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አጀማመር/ አመጣጥ
3) በደርግ አገዛዝ ስር የፓርቲዎች ይዞታና የአደረጃጀት መልክ
4) በህወሃት/ኢሕአደግ አገዛዝ ሰር የፖለቲካ አደረጃጀት ምን ይመስላል
5) በዶ/ር አቢይ እየተመራ ባለው የሽግግር ወቅት ምን ዓይነት የፖለቲካ አደረጃጀት ይታያል
6) የነገው አደረጃጅት ምን ቢሆን ይሻላል

## 1) በንጉሳዊ አገዛዝ ዘመን ፖለቲካና የፓለቲከኞች ሁኔታ ምን ይመስል ነበር

ኢትዮጵያ ለበርካታ ምእተ ዓመታት፣ በተለያዩ ስርወ መንግስታትና ነገስታት ስትገዛ የቆየች ለመሆኗ፣ ብዙ የአገር ውስጥና የውጭ ታሪክ ጸሃፊዎች መዝግበዋል። ንጉሶች ባልደረሱበት ቆሮዎችና ኡጋዞች ሲገዙ እንደነበር ይታወሳል። የአገሪቱ ድንበሮች ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታው በሚፈቅደው መጠን ሲሰፋና ሲጠብ የቆየ ቢሆንም፣ መንግስት ግን ከጥንት ጀምሮ እንደነበር ተጽፏል። መንግስት እስካለ ድረስ ፖለቲካ እንዳለም መገመት ይቻላል፤ ይሁን እንጂ ከ1966 ዓ.ም. በፊት

በአገራችን የነበረው ፖለቲካ አሁን ካለው ፖለቲካ ለየት ያለ እንደነበር ይወሳል። ቀደም ባሉት ዘመናት እንኳን በኢትዮጵያ በአውሮፓም ተንሰራፍቶ የቆየው ንጉሳዊና አሃዳዊ አግዛዝ እንደነበር ታሪክ መዝግቦታል። ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ በስተቀር በመላው አውሮፓ ፖለቲካ በፓርቲ መመራት የጀመረው በ19ነኛው ክፍለ ዘመን ነበር ቢባል ስህተት አይሆንም። ይህም በዋናነት ከሠራተኞች እንቅስቃሴና ከግራው የፖለቲካ ፍልስፍና ጋር ተዳምሮ የመጣ ለመሆኑ ብዙ ምልክቶች አሉ። ስለሆነም ከ1966 ዓም በፊት በኢትዮጵያ የነበረው መንግስት/አገዛዝ፤ ከአውሮፓ አንድ ምእተ ዓመት የዘገየ ቢሆንም፤ ሌሎች አገሮች ውስጥ ከነበሩ አስተዳደሮች/አገዛዞች የተለየ እንዳልነበረ ግልጽ ነው።

እዚህ ላይ ፓርቲ ባልነበረበት ዘመን መንግስት እንዴት ሊለዋወጥ ይችላል ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። በብዙ አገሮች፤ መለኮታዊ ሥልጣን አለን የሚል ሽፋን ፈጥረው፤ ስርወ መንግስት ተክለው፤ መንግስትን/አስተዳደርን ከአባት ወደ ልጅ ሲያሸጋግሩ ኖረዋል። ሌሎች ደግሞ ወይ በጉልበት ወይ በዲፕሎማሲ ወይ በታዋቂነት ጎልተው የሚታዩ በመሆናቸው፣ የመግስትን ስልጣን ከአንድ ቤተሰብ እንዳይወጣ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ይህ ክስተት በሰለሞንና በዛጐዌ ስርወ መንግስታት፤ እንዲሁም በደቡብ ኢትዮጵያ በተለያዩ የነገስታት ዝርያዎች ዘንድ ሲሰራበት የቆየ አካሄድ ነው። በቀድሞው አውሮፓም ልክ ከዘመነ መሳፍንት በፊት እንደነበረችው ኢትዮጵያ ይህ ክስተት በጉልህ ታይቷል። ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉት የመንግስት ለውጦች በሰላምና በታላቅ ድግስ የሚከበሩ እንደነበር ይታወቃል።

ባለፉት ዘመናት ሌላው የመንግስት አለዋወጥ ሂደት ኃይልን መሰረት ያደረገ ነው። የብዙ አገሮች ታሪክ እንደሚያሳየው የመንግስት ለውጥ በነውጥ፤ እስከ ጦርነት በሚሄድ የሃይል ድርጊት ሲከናወን እንደኖረ ተጽፏል። አንዱ ልዑል ወይም ንጉሥ፣ በወታደር ብዛት፣ በመሳሪያ ዓይነት፣ በግዛት ስፋት፣ በቀለብ አቅርቦት ሲበረታ፤ ጎረቤቱ ያለውን ልዑል ወይም ሲገብርለት የቆየውን ንጉስ በጦርነት ገጥሞ፣ ካሸነፈ በትረ መንግስቱን ይይዛል፤ ግዛቱንም ወደ ራሱ ግዛት ይጠቀልላል። ሌሎች ጉዳዮች ተደማምረውም ቢሆን በአውሮፓ የ30 ዓመታት ጦርነት፣ የመቶ ዓመታት ጦርነት ተብለው የሚታወቁት የታሪክ ዘመናት በዚህ ዓይነት በተካሄዱ የመንግስት ለውጦች የሚታወሱ ናቸው። በአገራችንም ዘመነ መሳፍንት ተብሎ የሚታወቀው የታሪክ ክፍል በኃይልና በጦርነት የታጀቡ የመንግስት ለውጦች ሲካሄዱ የነበሩበት ጊዜ መሆኑ የሚታወስ ነው። እስከ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ያለው ጊዜ በከፊልም ሆነ በሙሉ ይኸው ባህሪ ተንጸባርቆበታል። በአገራችን ከአጼ ቴዎድሮስ በኋላ እስከ ሐይለስላሴ ዘመነ መንግስት፣ ንጉሶች በአመዛኙ በሰላማዊ መንገድ የመንግስት ሥልጣን ሲለዋውጡ ቆይተዋል፡፡

በቀድሞው ጊዜ በአውሮፓም ሆነ በኢትዮጵያ፣ በንጉሳዊ አስተዳደር ዘመን ፓርቲ የለም፤ የስልጣን ክፍፍል የሚባልም ነገር የለም፤ ስልጣን ሁሉ ተሰብስቦ በንጉሱና በባለሟሎቹ እጅ ነው። ሸንጎም፣ ዳኝነትና ፍትህ፣ አስተዳዳሪም፣ የጦር አዝማችና ጄኔራልም ንጉሱ ነበር። ስለሆነም በቀድሞው ንጉሳዊ አስተዳደር የዛሬው ዓይነት ዴሞክራሲ በፍጹም አይታወቅም። አንዳንድ በበጎ አድራጎት የተነሳሱ ንጉሶች የአማካሪ ሸንጎ (ካውንስል) እንደነበራቸው ተጽፏል። ይህም ቢሆን ለንጉሶቹ የውሳኔ አሰጣጥ ምቾት ታስቦ የሚደረግ እንጂ ከህዝብ አሳታፊነትና ከፍትሃዊ አስተዳደር ጋር እንደማይገናኝ ይታወቃል።

## 2) በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አጀማመር (የየካቲት አብዮት)

የ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት እንደ ታሪካዊ ክስተት ከሚታይባቸው ጉዳዮች አንዱ በአገሪቱ የመጀመሪያዎቹ ፓርቲዎች በዚህን ጊዜ መመስረታቸው ነው። በአብዮቱ ዘመን ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ዜጎች የተዋቀሩና የኢትዮጵያን ግዛታዊ ሉዐላዊነትና የሕዝቧን ታሪካዊ ትስስር መሰረት ያደረጉ ሁለት ፓርቲዎች ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ አሉ - ኢሕአፓና መኢሶን። በማንኛውም መስፈርት ቢለካ ይህ ክስተት የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለማዘመን የተወሰደ የመጀመሪያ እርምጃ ነው ቢባል ከውነት የራቀ አይደለም። የመስራቾቹ ቀዳሚ ዐላማ አገሪቱን ከፈላጭ ቆራጭ ንጉሳዊ አስተዳደር ወደ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ ለማሸጋገር፣ ውድድርና ሙሉ መብት የሚገለጽበት፤ የአገሪቱን ፖለቲካ ከአውሮፓና ከአሜሪካ እኩል የሚያስቀምጥ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመፍጠር ነበር። ይሁን እንጂ ደርግ የተሰኘ የምርጥ መኮንኖች ቡድን የአብዮቱን ህዝባዊ ባህሪ ቀይሮ፤ ንጉሱን በአመጽ አውርዶ፤ ወታደራዊ አምባገነን መንግስት ሲያውጅ፤ በፓርቲዎች መመስረት የተጀመረው የለውጥ ሂደት ወደ ታለመለት ግብ ደርሶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገሪቱ እንዳይመሰረት ተጨናገፈ።

ደርግም መጣ ሌላ ከአብዮቱ በኋላ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መሠረታዊ በሆነ ደርጃ ተቀየረ። ንጉሳዊ ሥርዓት ሊመለስ በማይችልበት መንገድ ከፖለቲካ መድረኩ ላይ ተሰናበተ። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያውያን የትኛውን ፓርቲ ልምረጥ

ብለው ሲያስቡ እንጂ ማንን ላንግስ ብለው ሲጨነቁ ተሰምቶም አይታወቅ። ከ1966 ዓም በኋላ ኢሕአፓና መኢሶን በቀደዱት ፈር ወደፊት መጓዝ እንጂ ወደኋላ መመለስ በፍጹም የሚታለም ሆኖ አልታየም። ላለፉት 44 ዓመታት የጭቆናና የአፈና አገዛዝ በአገራችን ላይ የዘረጉት የደርግና የወያኔ መንግታት እንኳን፤ በፖለቲካ ፓርቲ ስም ነበር አገር ሲበድሉና ሲመዘብሩ የቆዩት። ሆኖም ግን ህዝቡም ሆነ የፖለቲካው ልሂቃን በፓርቲ መደራጀትን፣ የተለያየ ርእዮት አንግበው፣ የተለያየ ዐላማ ደርድረው፣ ተለዋጭ ለሆነ የመንግስት ስርዐት መታገልና መከራከር ዘመኑ የሚፈቅደው የፖለቲካ አሰላለፍ ነው ብለው ተቀብለውታል፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ይህን አካሄድ የሚያስቀይር አስተሳሰብ ከህዝቡም ሆነ ከፖለቲካው ልህቃን ዘንድ አይደመጥም፡፡

## 3) በደርግ ዘመን የፖለቲካ አደረጃጀት

ደርግ የተሰኘው የመኮንኖች ቡድን ተቃዋሚውን ሁሉ በሃይል ደፍጥጦ ለ17 ዓመታት በግፍና በሰቆቃ አስተዳደረ፡፡ በመጀመሪያዎቹ የደርግ አገዛዝ ዓመታት አገሪቱ የፖለቲካ አደረጃጀት ቤተ_ሙከራ ሆና መቆየቷን ስለዘመኑ የተጻፈው ታሪክ በግልጽ ያሳያል፡፡አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ፣ ደርግ ስልጣን ከህዝብ እጅ ነጥቆ በትረ-መንግስቱን ከተቆጣጠረ በኋላ፣ ሶስት ዓይነት የአደርጃጀት አቅጣጫዎች ተከሰቱ፤ እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን፣ በዚያን ጊዜ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ስለነበረች፣ ከአብዮቱ በፊት በኤርትራ ወስጥ ህልወና የነበራቸው ሁለት ጎላ ጎላ ያሉ ድርጅቶች እንደነበሩ ማውቅ ተገቢ ይሆናል - መጀመሪያ ELF በኋላም EPLF. እነዚህ እንግዲህ ፓርቲ ባይሆኑም የፖለቲካ ድርጅቶች መሆናቸውን ተገንዝቦ ማልፍ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚያም በተጨማሪ በዋናው የኢትዮጵያ ፖለቲካ መድረክ ላይ ያሳደሩት ተጽእኖ ከፍተኛ በመሆኑ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሲወራ፣ ኤርትራ ከውስጥ ወይም ከጎን ብቅ ማለቷ እንደማይቀር ማስተዋል ይገባል፡፡

1) በደርግ ድጋፍና እውቅና የተደራጁ ትናንሽ፣ አገር አቀፍ አመእካከት የነበራቸው ፓርቲዎች (በኋላ ኢማሌድህ በሚል ህብረት ወስጥ የተጠቃለሉና ተራ በተራ በደርግ የተበሉ/ህልውናቸው የጠፋ)፡፡ ከነዚህ ውስጥ በስም የሚታወቁት ፤ መኢሶን፣ ቀይ ባንዲራ፣ ኢጭአት፣ ሰደድና ማልሬድ ሲሆኑ ሁሉም የግራውን ፖለቲካ የሚያራምዱ፣ ከሰደድ በስተቀር ሁሉም አገር ወዳድ በሆኑ ምሁራን የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ከመካከላቸው ጎላ ያለው፣ በርካታ አባላት የነበሩትና አገር አቀፋዊ ተጽእኖ ለማሳደር የሚችል አቅም የነበረው መኢሶን ብቻ ነው፡፡ ከዚያም በላይ መኢሶን ቀደም ብሎ የተቋቋመና በሳል አመራር የነበረው ሰለመሆኑ ይነገራል፡፡

2) ከደርግ እውቅና ውጪ፣ በህቡእና በይፋ የተደራጁ፣ አገር አቀፋዊ አመለካከት የነበራቸው ሁለት ፓርቲዎች ነበሩ፡፡ አብዮቱ እንደፈነዳ በከፊል ይፋ ሆኖ ወደ ፖለቲካው መድረክ የዘለቀው ኢሕአፓ ከደርግ የሚሰነዘረው ግድያና እመቃ ለህልውናው የሚያሰጋው ሆኖ በመገኘቱ ከ1972 ዓም በኋላ ሙሉ በሙሉ ህቡእ ገባ፤ ከፊሉን አባላቱን ወደ ትጥቅ ትግል አሰማርቶ ደርግን በመሳሪያ መፋለም ጀመረ። ኢሕአፓ በአፍላ ዘመኑ በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ አባላትና እስከ ትንንሽ መንደሮች ድረስ የሚዘልቅ መዋቅር የነበረውና ሰፊ ህዝባዊ ድጋፍ የተቸረው ድርጅት እንደነበር ይነገራል። አብዛኛዎቹ አባላቱ ቀይ ሽብር ተብሎ በሚታወቀው የደርግ የጥቃት ዘመቻ ተገድለዋል፣ ታስረዋል ወይም ተሰደዋል። ይህ ፓርቲ እንደ መኢሶን ሁሉ የግራ ርእዮተ ዓለም የሚከተል ቢሆንም፣ ሁለቱ በዋናነት በደርግ መንግስት ላይ የነበራቸው አቋም ስለተለያየ፤ ወደ መጠላለፍና ወደ ጸብ ዞሩ፣ የነዚህን ጸብ ብዙ ጸሐፊዎች በዘመኑ የአገራችን የፖለቲካ ታሪክ ላይ ያረፈ ጎጂ ጠባሳ ነበር ይሉታል።

   ሁለተኛው አገር አቀፍ አመለካከት የነበረውና ገና ከጅምሩ ከደርግ መንግስት ጋር ተጋጭቶ ወደ መሳሪያ ትግል የገባው ፓርቲ ኢዴህ ነበር። ይህ ፓርቲ አብዮቱን የሚቃወም፣ እንዲያም ሲል ንጉሳዊ አስተዳደር እንዲመለስ የታገለ ሲሆን የተቋቋመውም በወደቀው መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣኖች ነበር። ኢዴህ በዚህ ዘመን ከተመሰረቱ ፓርቲዎች ብቸኛው የቀኝ ክንፍ ፓርቲ እንደነበር ይታወሳል። ኢሕአፓና ኢዴህ፣ እነኚህ ሁለት አንጋፋ ፓርቲዎች የቆሙለት መሰረተ ዓላማ የተለያየ ቢሆንም፤ ደርግ በጠላትነት ፈርጆ ስለሚያሳድዳቸው፤ እራሳቸውን ከጥፋት ለማዳን ወደ ትጥቅ ትግል ተሰማሩ። ቀደም ሲል ባይጣጣሙም ትግሉ እየመረረ ሲሄድ፣ ኢዴህ ከትግሉ ሜዳ እስከሚወጣ ድረስ በትብብረ ሲታገሉ ቆይተዋል።

3) በጎሳ/በብሄረ_ሰብ ስም መደራጀት በደርግ ዘመነ መንግስት ተባብሶ ቀጠለ፡፡ መገንጠልን ዓላማ አድርገው ሲንቀሳቀሱ የቆዩ ድርጅቶች በቀድሞው የኤርትራ ክፍለአገር እንደነበሩ ቀደም ሲል ተጠቅሷል፤ በደርግ ዘመነ መንግስት በጎሳ የመደራጀት ክስተት በድቡብና በምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ተስፋፋ፡፡ በዚህ ዘመን የተመሰረቱ የብሄርሰብ/የጎሳ ድርጅቶች መገንጠልን ዓላማ ያደረጉ እንደነበር ከስማቸውና ከታሪካቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ጎላ ጎላ ያሉት ሕወሃት ፤ ሱማሌ አቦ (በኋላ ወደ ኦነግ የተለወጠው)፣ ምእራብ ሱማሌ ነጻ አውጪ(በኋላ ወደ ኦብነግ የተለወጠው)፤ የሲዳማ ነሳ አውጪ ግንባር (የሚገርመው እነዚህ ድርጅቶች አሁንም በዚሁ ስማቸው እየተንቀሳቀሱ መገኘታቸው ነው)፡፡ ለነዚህ የጎሳ ድርጅቶች መመስረት ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደነበሩ ይጠቀሳል፤ አንደኛው የደርግ ግፈኛ መንግስት በህዝብ ላይ የጫነው መጠነ ሰፊ የጭቆና አገዛዝ፣ በቋፍ ለነበሩ የጎሳ ልህቃን፣ ጭቆናው በነሱ ህዝብ ላይ ብቻ እንደወደቀ አስመስለው ለማቅረብ ስላመቻቸው፤ ህዝቡን ተነስ ብለው ቀሰቀሱ፣ አደራጁ፡፡

ሁለተኛ የአካባቢው መንግስታት፣ በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር የጂኦፖለቲካ ቅራኔ ያላቸው፣ በአገሪቱ ውስጥ አብዮት በመፈንዳቱና የመንግስት ለውጥ በመደረጉ አገሪቱን ለማደከም መልካም አጋጣሚ ነው ብለው ስለገመቱ የነጻ አውጪ ድርጅቶችን ማስታጠቅና መርዳትን ከሌላው ጊዜ በላቀ ትኩረት ተያያዙት፡፡ በዚህ ዘመን የሱማሌ ሬፑሊክና ግብጽ የጎሳ ድርጅቶችን በማደራጀትና እርዳታ በማቅረብ ጎላ ያለ ሚና ሲጫወቱ ነበር፡፡ በተለይም በሰይድ ባሬ የሚመራው የሶማሌያ መንግስት 5ቱን የሶማሌ ግዛቶች ለማሰባሰብ ጊዜው አሁን ነው ብሎ በማሰብ፤ የኦሮሞን ልጆች ሶማሌ አቦ ብሎ አደራጀ፤ እንዲሁም የኦጋዴንን ተውላጆች የምእራብ ሶማሌ ነጻ አውጪ ብሎ አደራጅቶ ላከ፡፡ ይህም አልበቃ ብሎት ከምእራቡ ሃያላን መንግስታት ጋር ተባብሮ በ1969 ዓም አገሪቱን በቀጥታ ውረረ፡፡ በሶስተኛ ደረጃ በጦርነት ልምምድም ይሁን በድርጅት ተጠናክረው የነበሩት የኤርትራ ነጻ ኣውጭ ግንባሮች የመገንጠል እንቅስቃሴዎች በአገሪቱ ውስጥ እንዲበራከቱ ትልቅ አስተዋስኦ አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ ሕወሃትና በምስራቅም አንዳንድ ድርጅቶች የሰለጠኑትና የታጠቁት ኤርትራ እንደነበር ይነገራል፡፡

ለማጠቃለል ያህል በደርግ ዘመን የፖለቲካ አደረጃጀት፣ እስከዚያን ጊዜ በነበረው የአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በስፋትና በዓይነት ተበራክቶ የታየበት ጊዜ ነበር፤ በዚያን ዘመን የተፈጠሩ ድርጅቶች የሚከትሉት ባህሪያት ነበሯቸው፡-

1) በከፊል አገር አቀፍ፣ በከፊል የጎሳ ድርጅቶች ነበሩ (ኢሕአፓ፣ መኢሶን፣ ኢዴሀና ኢሠፓ አገር አቀፍ ፓርቲዎች ሲሆኑ፤ ሕወሃት፣ ኦነግ፤ ኦብነግና የሲዳማ ነጻ ውጪ ድርጅት የጎሳ ድርጅቶች ነበሩ)።
2) በርእዮተ ዓለም በኩል ኢዴሀ ብቻ የቅኝ ርእዮተ ዓለም ተከታይ ሲሆን ሌሎቹ በአመዛኙ ከተማሪው ንቅናቄ የመነጩ ማርክሲስቶችና ግራ ዘመም ድርጅቶች ናቸው።
3) ኢሠፓ ብቻ በደርግ የተቋቋመና የተደገፈ ህጋዊ ፓርቲ ሆኖ እስከ ደርግ ፍጻሜ ድረስ ሲቀጥል፣ ሌሎች ድርጅቶች በሙሉ፣ ህገ ወጥ ተብለው በስደትና በህቡእ እስከ 1983 ዓም የቆዩበት ጊዜ እንደነበር ይታወሳል። አንዳንዶቹ እንዲያውም የአገራቸውን መሬት መርገጥ የቻሉት በዚህ በያዝነው በ2011 ዓም ነው።

## 4) በሕወሃት/ኢሕአዴግ ዘመን የፖለቲካ አደረጃጀት

ይህ ዘመን ከ1983 እስከ ሚያዝያ 2010 ዓም ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ነው፡፡ በዚህ ዘመን የተካሄዱት የመደራጀት ጥረቶች ቀደም ብለው ከነበሩት በሁለት መንገድ ይለያሉ፡-
አንደኛ ጥረቱ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፤ ይህም አገራዊ ድርጅቶችንና ተቋሞችን እያኮሰሰና እያጫጫ በብሄረ-ሰብ መደራጀት ብቸኛው የፖለቲካ አደረጃጀት መሆኑን የሚሰብክ አካሄድ ታቅዶ ስራ ላይ የዋለበት፤
ሁለተኛ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ አዲስ የፖለቲካ ምህድስና በገዢው ፓርቲ ተገፋፍቶ ስራ ላይ መዋሉ፤ ማን ቀረ በሚያሰኝ መልክ በእያንዳንዱ ቋንቋና ብሄር-ሰብ ስም የፖለቲካ ድርጅት በማቋቋም ምድሪቱ በትንንሽ አጃቢ ቡድኖች እንድትሞላ መደረጉ።

ይህ አካሄድ እንደገና በአገሪቱና በህዝቧ ላይ ሁለት ከባድ ከባድ ውጤቶች አምጥቷል። ሁለቱም በጣም አደገኛ ውጤቶች ናቸው፡-

አንደኛ አገር አቀፍ ፓርቲዎች በመዳከማቸው ምክንያት፤ ገዢው ፓርቲ በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ላይ ብቸኛው ተዋናኝ እንዲሆን ስለረዳው፣ ያው እንዳየነው ለ27 ዓመት የናጠጠ አምባገነንነት ተንሰራፍቶ ቆየ። በተጠርጣሪ ላይ ጥፍር እስከ መንቀልና ሽንት እስከ መሽናት የዘለቀ የግፍ አገዛዝ ከመንገሱም ባሻገር፣ መንግስትና ገዢው ፓርቲ አንድ በመሆናቸው የአገሪቱ ሃብት ለቁጥር በሚታክት መጠን ተመዘበረ። ይህም ብቻ አይደለም፣ የአገር አቀፍ ፓርቲዎች መዳከም ሌላም መዘዝ አስከተሏል፤ ሰላማዊ የሆነ የስልጣን ሽግግር ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ አስቸጋሪ አድርጎታል። እንዴት ቢባል የገዢው ፓርቲ እንዲህ በሚዳከምበት ጊዜ፣ እሱን ተክቶና አገሪቱን ከዳር እስከ ዳር አቀራኝቶ ሊያስተዳድር የሚችል ጠንካራና አስተማማኝ ድርጅት እንዳይኖር አድርጓል፡፡ ይህ በራሱ የአገር ጸጥታና የህዝብ ደህንነት እንዲታወክ ምክንያት በመሆኑ ሰርዐት አልበኝነት ነግሶ አሁን የሚታየው አለመረጋጋት እንዲከሰት ሆኗል።

ሁለተኛ በአገራችን ለተንኮልና ለሴራ ፖለቲካ ከፊት ቀድሞ የመራው ሕወሃት ቢሆንም፣ ሌሎችም የጎሳ ልህቃን የሱን ፈር ተከትለው የዘረፋውና የጭቆናው አጃቢ ሆነው ቆይተዋል። ሕወሃት ደግሞ ጠንካራ አገራዊ ድጋፍ ስላልነበረውና ዓላማውም መገንጠልን የሚያቀነቅን ስለነበር፤ በምራባውያን ድጋፍ ስልጣን በጁ ቢውድቅም፤ በምን መንገድ ስልጣኑን በቁጥጥሩ ስር ሊያቆይ እንደሚችል ማሰብ ነበረበት፤ ኢትዮጵያ የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች አገር መሆንዋን የተረዳው ሕወሃት፣ በዚህ ገጸ ባህሪዋ ውስጥ ለሱ በገዢነት የመቆየት ምኞት ምን ፋይዳ ሊያገኝበት እንደሚችል ተንኮል ባዘለ ልቦናው ተመራመረ። አስቦም በጎሳ ማደራጀት ብቸኛው መፍትሄ መሆኑን ደረሰበት።እናም ዛሬ ከመንግስት ድረ ገጾች እንድምናነበው በአገሪቱ ውስጥ ከ90 ያላንሱ የጎሳ ድርጅቶች እንደ አሸን እንዲፈሉ አደረገ። ዴሞክራሲው ቢኖር መቼም ይሁን ሊባል ይችል ነበር፤ ነገር ግን ከደህንነቱ እስከ ጦር ኃይሉ፣ ከሚኒስተሩ እስከ ፓርላማው፣ ከሬዲዮ እስከ ቴሌቪዢን፤ ከቴሌ እስከ ኤልፓ ፣ ከቸርቻሮ እስከ ጅምላ ንግድ በአንድ ቡድን፣ በሕወሃት/ኢሕአደግ ብቻ ተቆልፎ በተያዘበት አገር ትንንሽ የብሄረሰብ ፓርቲዎች የገዢው ቡድን አጫፋሪ ከመሆን አልፈው ለህዝባቸው ያስገኙት ተጨባጭ ጥቅም የሚታይ አይደለም፡፡ ገና ከጠዋቱ አልተነገራቸውም እንጂ ሕወሃት በርካታ ፓርቲዎች ሲያደራጅ በአገሪቱ ላይ የያዘውን ስልጣን በበላይነት ለመምራት እንዲያስችለው ታስቦ፤ የፖለቲካ ዳይናስቲውን እድሜ ለማራዘም ታቅዶ እንደነበር ግልጽ ነበር። አንዳንዶች ይህን ደባ ነቅተው ድምጽ ማሰማት ሲጀምሩ፣ እንደ ዶሮ እየታነቁ ወደ ቂሊንጦ ሲወረወሩ እንደነበር የሚታወስ ነው።

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት እንዳየነው እነዚህ ድርጅቶች በአገሪቱ የፖለቲካ ህይወት ውስጥ ምንም ሚና አልነበራቸውም፤ በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈጻሚውም ሆነ በሕግ ተርጓሚው አካል ውስጥ ተሳትፎ የላቸውም። እራሳቸውንም ችለው ምርጫ አይወዳደሩም። ስልጣን ሙሉ በሙሉ በሕወሃት/ኢሕአደግ መዳፍ ውስጥ ስለቆየ በአሁኑ ሰዓት እነዚህ ፓርቲዎች ሕወሃት ለምን ጉዳይ እንዳቋቋማቸው በሚገባ ይረዳሉ የሚል ግምት መውሰድ ይቻላል። ነገር ግን ምናልባት ለነሱም በግልጽ የማይታይ፣ በሕወሃት ስሌት ውስጥ ግን እንደ ፕላን ቢ የተያዘ አደገኛ እቅድ እንዳለ አሁን እየታየ መጥቷል። ከላይ እንዳየነው ሁኔታው እስከፈቀደ ድረስ ሕወሃት እነዚህን ፓርቲዎች (አንዳንዶች ዞምቢ ፓርቲዎች ይሏቸዋል) ትርፍራፊ እየጣለላቸው ሰልፍ አድማቂ ሆነው እንዲያጅቡት ሲያደርግ ቆይቷል። አሁን ግን ሕወሃት ዳይናስቲውን ለማስቀጠል ሁኔታው ስላልፈቀደለት ፕላን ቢ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየተመዘዘ መውጣት ጀምሯል።

የሕወሃት ፕላን ቢ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ያለችውን አህያ ብሂል የሚከተል ነው፤ ለዚህም ነው ገና ከጅምሩ ፓርቲዎች በጎሳ እንዲደራጁ፣ አስተዳደር በቋንቋ እንዲከለል በሕገ - መንግስት አጽድቆ ላለፉት 27 ዓመታት አገር ያስተዳደረው። ይህም አደረጃጀት ጎረቤት ከጎረቤት እንዲቃረን፤ ሰሜን ያለው ህዝብ ደቡብ ካለው ጋር እንዳይገናኝ ተደርጎ የተዋቀረ ስለሆነ አገሪቱን በማያባራ ትርምስ ውስጥ እንድትገባ ታስቦ ተግባር ላይ ውሏል። በህወሃት ዘመን የተወለደ ሰው ከዚህ ሌላ አደረጃጀት እንዳያውቅ ተደርጓል። አሁን እንደሚታየው በአገሪቱ የተለያዩ ግዛቶች፣ የማንነት ጥያቄ፣ የድንበር ጥያቄ፤ የክልል ጥያቄ በየእለቱ ሲነሳ ይታያል። ከዚያም አልፎ አንዱ ህዝብ ሌላውን፣ አንተ ከዚህ አይደለህም ውጣልኝ፤ ይህ የኔ ግዛት ነው መልስልኝ የሚሉ በርካታ ጸቦችና ውዝግቦች በየስርቻው

እንዲበራከቱ ሆኗል። ሕወሃት በሚገዛበት ጊዜ እንዲህ አይነት ጥያቄዎች በብዛት አይነሱም ነበር፤ አሁን ዴሞክራሲው የተሻለ ሆኖ ሳለ፤ እንዲህ ያሉትን ጥያቄዎች ምን አበራከታቸው ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል። ከላይ እንደተገለጸው እነዚህን በየጎጡ የሚጫሩ አመጾች ከሕወሃት ፕላን ቢ ነጥሎ ማየት ያስቸግራል።

ሕወሃት ፖለቲካውን ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚውንም ሲቆጣጠር የቆየ በመሆኑ፣ በየጎጡ በሱ አምሳል የተቀረጹና ገንዘብ፣ መሳሪያ፣ ሌላም አገልግሎት የሚቀርብላቸው ወኪሎች አስቀምጧል። እነዚህ ናቸው እንግዲህ አሁን በየብሄረሰቡ ውስጥ ተሰግስገው የሕወሃትን ተልእኮ እየፈጸሙ ያሉት። ሰሞኑን እንዳየነው ሕወሃት ቤት አቃጥሉ ሲል መንደር ማጋየት፤ ማህበረ ሰቦችን አጋጩ ሲል፣ የቋንቋና የጎሳ ግጭቶች እየፈጠሩ ጎረቤታሞችን ማጋደልና ህዝብ ማፈናቀል የአገራችን እጣ ፈንታ ሆኖ ሰንብቷል። ይህ ሂደት ከቀጠለ በገሪቱ ህልውና ላይ አደጋ ከማስከተሉም በላይ ህዝቡም በሰላም እጦት ሰርቶ ማደር ይሳነዋል። ወያኔም ያምጣው ሌላም ቢመኘው፣ የጎሳ አደረጃጀትና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ አስተዳደር ውሎ አድሮ ለአገራዊ አንድነትና ለኢኮኖሚ እድገት ፈጽሞ የሚመች እንዳልሆነ አየነው፣ ኖርንበት፤ አጥፊ ነው። የፖለቲካ ልሂቃንም ሆኑ ህዝቡ ይህን አደጋ ተገንዝበው፣ የጎሳ አደረጃጀትን ከነ ፍልስፍናው ወዲያ ጥለው፣ ሁላችንንም የሚጠቅም አማራጭ አደረጃጀት መፈለግ ይኖርባቸዋል።

አንዳንዶች በተለይም ሕወሃት እንዲህ ያለውን አባባል ሲሰሙ "ፌዴሬሽን ይጥፋ" ማለት ነው ብለው ይጮሃሉ። አይደለም፣ የፌዴራል አወቃቀር ለአገራችን እንዲያውም በጣም ተስማሚ ሊሆን የሚችል አስተዳደር ነው፤ ይሁን እንጂ በሌሎች አገሮች እንደምናየው፣ ከጎሳና ከቋንቋ የጸዳ ሊሆን ይገባዋል። ስለ ፌዴራል አስተዳደር በሌላ ጽሁፍ እንመለስበታለን።

## 5) በዶ/ር አቢይ የሽግግር ወቅት ምን ዓይነት አደረጃጀት ይታያል

አሁን ያለው መንግስት ባመጣቸው ለውጦች ልክ የሚመዘን ከሆነ አብዮተኛ ሊባል የሚችል ቢሆንም፣ በተወሰነ ደረጃ ግን የሕወሃት/ኢሕአደግ መንግስት ቅጥያ መሆኑ ግልጽ ነው። ለምሳሌ ገዢው ፓርቲ አሁንም ኢሕአዴግ ነው፤ አጥፊው ሕገ-መንግስት አሁንም አልታገደም፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ በጎሳና በቋንቋ ላይ የተመሰረቱ የፖለቲካ ድርጅቶች አሁንም የፖለቲካውን ምህዳር እንደተቆጣጠሩት ነው ። እልፍ ስንል ደግሞ የዚህና የዚያ ነጻ አውጪ ግንባሮችም አሉ። (ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ ገና አሁን ወደ አገር ገብተው መንቀሳቀስ የጀመሩ በመሆናቸው ከወቀሳ በፊት ጊዜ ሰጥተን ወዴት እንደሚሄዱ ማየት ተገቢ ነው)። ስለሆነም በሽግግሩ ዘመን ሙብት የተከበረ ቢሆንም በአደረጃጀት በኩል እስካሁን ለውጥ የለም።

ይሁን እንጂ በሕወሃት ዘመን አጥልሞን የቆየው የጨለማ ድባብ ተገፎ፤ የብርሃን ጮራ መፈንጠቅ ጀምሯል። ይህ የብርሃን ጮራ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ክስተቶች ዙሪያ በጉልህ ይታያል፡-

1) የፖለቲካው ምህዳር በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅግ በሚያረካ መጠን ሰፍቷል፤ ለብዙ ዓመታት ሕገወጥ ተብለው በስደት የቆዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ አገራቸው ተመልሰው በሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ በቅተዋል፤ አገር ወስጥ የቆዩትም እንደልባቸው በይፋ መቀስቀስ፣ መደራጀት፤ መሰብሰብና መመልመል ችለዋል። በመንግስትና በገዢው ፓርቲ ላይ ያሏ_ፍርሃት ሂስ ሲያቀርቡና ሃሳብ ሲሰነዝሩ ይደመጣሉ፡፡
2) የአገር አቀፍ ፖለቲካ አራማጆችና የአንድነት ሃይሎች ስለ አገራዊ አንድነትና ሰለ ብሄራዊ እርቅ በሽብርተኛነት ሳይከሰሱ በአደባባይ መናገርና መስበክ የሚያስላቸው ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በጎሳ ትርክት ብቻ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተጨናንቆ የቆየው የአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ለአገራዊ የፖለቲካ ትርክት በድንገት በሩን ብርግድ አርጎ እንዲከፍት ተደርጓል፡፡ ለእድሜ ጠገቡ ህብረተሰብ ይህ የአገር አቀፍ ፖለቲካ ብሂል አዲስ ባይሆንም፤ አዲሱ ትውልድም በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ መማር እንደቻለና እየወደደውም እንደመጣ ግልጽ እየሆነ ነው።

3) የዶ/ር አቢይ መንግስት የፖለቲካ እስረኞችን በመፍታት፣ የአስተዳደር፣ የፍትህና የደህንነት ተቋሞችን በማሻሻል፣ የሲቪክና የሰብአዊ ሙብቶችን በማስከበር የወሰዳቸው እርምጃዎች በአገሪቱ በሙሉ ታይቶ

በማይታወቅ ደረጃ የነጻነትና በራስ የመተማመን መንፈስ ፈጥሯል። (ያም ሆኖ የኦሮሞ ፖለቲከኞችና ልህቃን የፌዴራል መንግስቱን ቁልፍ ቦታዎች መያዛቸው አነጋጋሪ ብሎም አስጊ ዝንባሌ መሆኑ ሳይዘነጋ);

4) የገዢው ግንባር ከጎሳ ድርጅትነት ወደ አንድ አገራዊ ፓርቲ ለመሸጋገር ያደረገው ውሳኔ ሌላው መልካም ዜና ነው፡፡ ይህ ውሳኔ በዚህ የሽግግር ዘመን ከተወሰኑ ትልልቅ ጉዳዮች አንዱ ነው ቢባል ከውነት የራቀ አይሆንም፡፡ ሆን ተብሎ በህወሃት የሚገፋውን የጎሳ ፖለቲካ ሲያስተናግድ ለሰነበተ አገር ይህ ዜና ንጹህ አየር እንደመተንፈስ የሚቆጠር ክስተት ቢሆንም፣ በይበልጥ ግን ለሌሎች የጎሳ ድርጅቶች የሚያሳየው አርአያነት ትልቅ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው።

## 6) ቀጣዩ አደረጃጀት ምን ይሁን

ከሚያዝያ 2010 በኋላ አገራችን ኢትዮጵያ አዲስ የተስፋ ጉዞ ጀምራለች። ይህ ጉዞ ለአገሪቱ ደማቅ ታሪካዊ ቁመና የሚመጥን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ወደ መገንባት ያደርሰናል ብለን እንመኛለን። ላለፉት 3 አስርት ዓመታት በሕወሃት የሚመራው መንግስት አገራችንን አዲስ የፖለቲካ ቤተ-ሙከራ አድርጎ ሲያባላን ሰንብቷል። የሕወሃት/ኢሕአዴግ ቤተ-ሙከራ አገራችን ላጋጠማት ተግዳሮት መድሃኒት ሆኖ አልተገኘም፤ እንዲያውም በሽታዋን ሁሉ አባብሶ ወደ ውድመትና ወደ ጥፋት አፋፍ እንዳደረሳት የሰሞኑ ብጥብጥ ጥሩ ማሳያ ነው። ማንኛውም ቤተ-ሙከራ ካልሰራ እንደሚወድቅ ሁሉ፣ በኛም ላይ የተሞከረውን የተንኮል ወጥመድ በቃ ብለን ነቃቅለን መጣል አለብን። በጎሳ መደራጀት፤ በቋንቋ መካለል ህዝብን የሚያናክስ አገርን የሚበትን ስለሆነ መቆም አለበት። የጎሳ ፖለቲካ ያየነው፣ የቀመስነው፣ የሞከርነው ስለሆነ አገራችንን ጠብቀን፣ ታሪካችንን አክብረን መኖር ከፈለግን ሁሉም ኢትዮጵያዊ አምዘግዝጎ ሊጥለው ይገባል፡፡

በጎሳ መደራጀትና በቋንቋ መካለል የሚያደርሰውን ጉዳት ከተመለከትን፣ የቀረው ጉዳይ ለአገራችን ዘለቄታዊ ጥቅም የሚሰጠው በምን መልክ መደራጀት ነው የሚለውን ማየት  ይሆናል፡፡ ይህን ለማወቅ ብዙ ማሰብና እሩቅ መሄድ አያስፍልግም፤ ከምስራቅ አፍሪካ ጀምሮ፤ አድማሳችንን እያሰፋን ዙሪያውን ብንመለከት፣ በየትኛውም ህብረተሰብ ፖለቲከኞች በጎሳ ተደራጅተው፤ የመንግስት ስልጣን ይዘው አገር የሚያስተዳድሩበት ቦታ እንደሌለ እናስተውላለን፡፡ ምናልባት በምሳሌነት የሚጠቀሱ አገሮች ቢኖሩ፤ በትጥቅ ትግል አሸንፈን ስልጣን ይዘናል በሚሉ ጥቂት አገሮች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በተቀረው ዓለም ሁሉ፣ በተለይም ዴሞክራሲ ባደገባቸው አገሮች፣ ፖለቲከኞች የተደራጁትና የሚደራጁት አገር አቀፋዊ ይዘትና ራእይ ባላቸው ምክንያታዊ ጉዳዮችና ርእዮት ዙሪያ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሁለት ጽንሰ ሃሳቦችን ግልጽ አድርገን እንለፍ፡- "አገር አቀፋዊ ይዘት" እና "ምክንያታዊ ጉዳዮች" ስንል ምን ማለታችን ነው፡፡

"አገር አቀፋዊ ይዘት" ሲባል ምን ማለት ነው? በአንድ በኩል በተወሰነ ድርጅት ውስጥ አባል የሚሆኑ ሰዎች ከአንድ አካባቢ ወይም ከአንድ የተለየ ቋንቋ ከሚናገር ማህበረሰብ ብቻ የተሰባሰቡ ሳይሆን፣ ከተለያዩ ክፍለ አገራት፤ ከተለያዩ ጎሳዎች፤ ቋንቋዎች ወይም ሃይማኖቶች የሚሰባሰቡ ናቸው ማለት ነው። በሁለተኛ ደረጃ የሚያሰባስባቸውም ዓላማ ለመላው አገርና ለሁሉም የአገሪቱ ህዝብ ጠቀሜታ ለማምጣት የታሰበ መሆን አለበት ማለት ነው። ለዚህም በአገራችን ውስጥና ከአገራችን ውጪ በርካታ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡- በአገር ውስጥ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ህብረት (ኢዴህ)፣ መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እነዚህ አገር አቀፍ ይዘትና ራእይ ያላቸው አገር በቀል ፓርቲዎች ናቸው። ከአገር ውጪ ለአብነት ያህል የእንግሊዙን የሰራተኞች ፓርቲ (ሌበር ፓርቲ)፣ የኬንያውን ካኑ (ኬንያን አፍሪካን ናሽናል ዩኒየን)፣ የሩሲያውን ዩናይትድ ራሽያና የህንዱን ኮንግሬስ ፓርቲ መጥቀስ ይበቃል።

"ምክንያታዊና ርእዮተ ዓለማዊ" ሲባል ምን ማለት ነው? ሰዎች በራስ አነሳሽነት ተሰባስበው የመንግስት ስልጣን ይዘው፣ የተወሰነ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራም ስራ ላይ ለማዋል ሲደራጁ ምክንያታዊ አደረጃጀት ይባላል፡፡ የዚህ አይነት አደረጃጀት ከዜግነት ፖለቲካ ጋር በቅርበት የተቆራኘ ከመሆኑም በላይ በመላው ዓለም ተቀባይነት ያለውም ይኸው አደረጃጀት ነው፡፡ ምክንያታዊና ርእዮተ-ዓለማዊ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ናቸው።

በዓለም ላይ በርከት ያሉ የርእዮተ-ዓለም ካምፖች እንዳሉ ይታወቃል፤ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ አገር አቀፍ ፓርቲዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት 4 ካምፖች ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው ፡-

1) የሶሻሊስትና የማርክሲስት ፓርቲዎች ካምፕ
2) የማህበራዊ ዴሞክራሲ ፓርቲዎች ካምፕ
3) የሊበራል ዴሞክራሲ ፓርቲዎች ካምፕ
4) የወግ አጥባቂ ፓርቲዎች ካምፕ

ከላይ የተመለከተው ዓይነት አደራደር ከቀኝ ወደ ግራ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚዘረዝር ነው፡፡ ግራ፣ ማእከልና ቀኝ፣ ተብሎ የፓርቲዎች አቋም መሰየም የተጀመረው በፈረንሳይ አብዮት ጊዜ ሲሆን ፓርቲዎች በምክር ቤቱ ውስጥ የተቀመጡበትን ቦታ የሚያመላክት ነበር፡፡ እስካሁን ድረስ ለሰራተኛው ህዝብ ጥቅም እንሚገታለን የሚሉ ፓርቲዎች የግራ ፖለቲካ አቀንቃኞች ይባላሉ፤ ሌላው ሁሉ ከነሱ ወደ ቀኝ ስለሚሆን ወይ ማእከለኛ ወይ ቀኝ ተብሎ ይፈረጃል፡፡ ጠቅለል ባለ አነጋገር ከላይ በሚታየው ዝርዝር ውስጥ ሶሻሊስቶችና ማርክሲስቶች የግራ ክንፍ ፓርቲዎች ሲሆኑ፣ ሊበራልና ማህበራዊ ዴሞክራሲ በማእከላዊነት ይመደባሉ፡፡ ወግ አጥባቂ ፓርቲዎች(ኮንሰርቫቲቭ) ሁልጊዜም የቀኝ ክንፍ ፓርቲዎች ሲሰኙ ቆይተዋል፡፡ በነዚህ ሰፋፊ ክፍፍሎች ውስጥ እንደየአገሩና እንደ ፖለቲካ ተቋማት እድገት እርከኖች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ አገሮች ሊበራል የሚባሉ ፓርቲዎች ግራ ዘመም ሲሆኑ፤ በሌሎች አግሮች ደግሞ ወደ ቀኝ ያደላሉ፤ ስልሆነም ሊበራሎች ንፋሱ ወደ ነፈሰበት የሚነፍሱ መሐል ሰፋሪ ይባላሉ፡፡ በርእዮተ ዓለም ላይ ተመስርተው የተቋቋሙ ፓርቲዎች በጣም የተለያዩ ስለሆኑ ብዙ ማለት ይቻላል፤ ወደፊት እንመለስበታለን፡፡

ለጊዜው ግን በርእዮተዓለም ላይ በተመሰረቱ ፓርቲዎች ላይ አንድ ነገር ብዬ ይህን ክፍል ልለፈው፡፡ ግራና ቀኝ በተለያየ የፖለቲካ ጫፍ ላይ የሚገኙ ፓርቲዎች እንደመሆናቸው መጠን፣ ግራዎች ለሰራተኛው ጥቅም የምንከራከር ተቋም ነን ይላሉ፤ በተቃራኒው ቀኞች ደግሞ ለአሰሪዎች በተለይም ለኮርፖሬሽኖችና ለትልልቅ ኩባንያዎች የቆሙ ናቸው ቢባል ከውነት የራቀ አይደለም፡፡ የቀኝ ፓርቲዎች ከሃብታሞች ጋር የሚጠለሉ በመሆናችው ጠንካራ የገንዘብና ድርጅታዊ አቅም አላቸው፡፡ ፕሮግራማቸው ጠቅለል ያለ በመሆኑ፣ ለአሰሪዎች እንደቆሙ አይናገርም፣ ፖለቲከኞች ካልሆኑ ተራው ሕዝብ በቀላሉ አይረዳቸውም፤ ስለሆነም ሰራተኛው ህዝብ ባልተደራጀባቸው አገሮች በተደጋጋሚ ምርጫ ሲያሸንፉ ይታያል፡፡ ለምሳሌ የተባበረችው አሜሪካ፡፡ ሊበራሎች እንደ ፔንዱለም ግራና ቀኝ መወዛወዛቸው የማይቀር ቢሆንም በብዙ አገሮች ውስጥ ለመካከለኛው የህብረሰብ ክፍል (ሚድል ክላስ ለሚሉት) ቆመናል ስለሚሉ ዴሞክራሲ በተስፋፋባቸውና ኢኮኖሚው ባደገባቸው አገሮች ተወዳጅ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ካናዳ፣ አውስትራሊያ ወዘተ..በሌላ በኩል ማህበራዊ ዴሞክራቶች ለመካከለኛውና ለዝቅተኛው ህብረተሰብ ክፍል እንደሚከራከሩ በግልጽ ፕሮግራማቸው ላይ ያሰፍራሉ፡፡ ይህን ርእዮት የሚከተሉ ፓርቲዎች በአውሮፓ፣ በላቲን አሜሪካና በእስያ ቅቡል ሲሆኑ በአፍሪካ ግን አምባገነንነት ነግሶ ያለበት ክፍለዓለም በመሆኑ ገና ቅጡ አልታወቀም፡፡ በሰሜን አሜሪካ እስካሁን አገራዊ ሰልጣን ይዘው መንግስት መስርተው አያውቁም፡፡ በካናዳ ግን በብዙ ክፍለ አገራት ምርጫ አሸንፈው የአካባቢ መንግስት ይመሰርታሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በግልጽ በፕሮግራማቸው ላይ ማህበራዊ ዴሞክራሲን እንከተላለን የሚሉ ሁለት ፓርቲዎችን እናውቃለን - ኢሶዴፓና ኢሕአፓ።

## ማጠቃለያ

እዚህ ላይ በአገራችን ውስጥ በርእዮተ ዓለም ዙሪያ የተደራጁ ፓርቲዎች አሉ ወይ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል፡፡ አጭሩ መልስ አሉ ማለት ቢሆንም፣ የፖለቲካውን መድረክ በዝርዝር መፈተሽ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ አገር ውስጥ ከቆዩት ውስጥ መኢአድ፤ ኢዴህና ኢሶዴፓ ይገኙበታል፡፡ ከውጭ የገቡት በርካታ ሲሆኑ፣ ለአብነት ያህል ጉልህ፣ ጉልህ የሆኑትን መጥቀስ ይበቃል፤ ከነዚም ወስጥ የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር፣ መድህን፣ ሩህ፣ ኢሕአፓና ግንቦት7 ይገኙበታል፡፡ ባለፍት ዓመታት ውስጥ በነዚህ ፓርቲዎች ላይ የተደረገው እመቃ፤ አሉ የሉም ከሚያሰኝ ደረጃ ላይ ያደረሳቸው ከመሆኑም ባሻገር የጎሳ ድርጅቶች መጎልበትና በብቸኝነት የመንግስት ድጋፍ ሰብሳቢ መሆን፣ ለአገራዊ ድርጅቶች መቀጨጭ ዋነኛ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሰሞኑን ከተለፈፈላቸው 107 ፓርቲዎች ውስጥ ወደ 80% የሚሆኑት የጎሳ ድርጅቶች እንደሆኑ ይታመናል፡፡ በቅንጅትና በአንድነት ስም የሚንቀሳቀሱትን የውሸት ግለሰቦች ከዚህ ስሌት ውስጥ አልጨመርኩም፡፡ በአንድ አገር ውስጥ ከሚገኘው የፖለቲካ ሃይል ወስጥ 80%ቱ እዚህና እዚያ ቆሞ በጥላቻና በጥርጣሬ የሚተያይ ቡድንተኛ ሲሆን አገራዊ ፖለቲካ የሚባል ነገር ሊተገበር ቀርቶ ሊታለም አይቻልም ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ከዚያም አልፎ በጎሳ ከተደራጁት ውስጥ የዚህና የዚያ ነጻ አውጪ ግንባር የሚባሉ መበራከታቸው የአገሪቱን ህልውና ስጋት ላይ የሚጥል ክስተት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። እንዲያም ሲል አሁን እንደሚታየው በየወረዳው ወደ መገዳደልና ወደ መፈናቀል የሚያደርስ ትርምስ

ወስጥ መግባት ብቻ ሳይሆን ብሎ ብሎ ወደለየለት ብጥብጥና የአገር መፍርስ መድረሳችን የማይቀር መስሎ እያስፈራራ ነው፡ ፡

ስለሆነም አገራችንን እንደ አገር ለማቆምና የህዝባችንን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ፣ በጎሳ መደራጀት ላይ የማያዳግም ውሳኔ መውሰድ ይጠበቅብናል፤ ልክ እንደጋና፣ ልክ እንደጎረቤት ኬንያ። በአንድ ዘመን መደራጀትም ሆነ ጎሰኛ ብሄርተኝነትን መምረጥ እንደሙብት ተቆጥሮ ሊሆን ይችላል፤ ከዛሬ አስር ወራት በፊት ኢትዮጵያን የሚያህል ትልቅ አገር በግንባር ቀደምትነት ሲያስተዳድር የነበረው ድርጅት “ሕወሃት - ሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ” - የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር- እንደነበር የሚታወስ ነው። አገር እያስተዳደሩ ወዴት ነጻ መውጣት እንደታለመ ማሰብ የሚቸግር ነው። ያን ሁሉ ትርምስ አልፈን ትንሽ ተስፋ መሰነቅ በጀመርንበት በአሁኑ ሰዓት እንኳን ሕወሃት ስሙን አልቀየረም፤ ዛሬም የነጻ አውጪ ድርጅት ነው። ይህ አካሄድና አደረጃጀት ደግሞ አገሪቱን ከመፍረስ አፋፍ ላይ እንዳደረሳትም አብሮ ሊታወስ ይገባል። መድሃኒት በሽተኛን ሊፈውስ እንጂ ለመግደል እንደማይሰጥ ሁሉ፤ በጎሳ መደራጀትም አገራችንን ወደ መፍረስ እያደረሳት በመሆኑ በአስቸኳይ ልናስብበት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ኢሕአደግ ወደ አገራዊ ድርጅት እራሱን ለመቀየር ያደረገው ውሳኔ እጅግ በጣም ሊወደስ የሚገባውና አርአያነቱም አገራዊ እርባና እንዳለው ደጋግሞ መናገር ተገቢ ነው። ከሁሉም በላይ ግን በደቡብ፣ በምስራቅና በምእራብ ኢትዮጵያ በሰፈሩ ትናንሽ ጎሳዎችና የቋንቋ ቡድኖች የተሰባሰቡ ድርጅቶች ቀልጥፈው ወደ አገራዊ ድርጅቶች መቀላቀል ወይም አዲስ አገር አቀፍ ድርጅት ውስጥ መሰባሰብ ለነገ የማያድር ተግባር መሆኑን ማሳሰብ እወዳለሁ። ሕወሃት ከ75 በላይ የጎሳ ድርጅቶችን በደቡብ ኢትዮጵያ ሲፈለፍል የግዛት ዘመኑን ለማስረዘም እንጂ ለህዝቡ ተቆርቁሮ እንዳልሆነ ከምን ጊዜውም ይልቅ ዛሬ ገሃድ እየሆነ መጥቷል። እነዚህ የጎሳ ድርጅቶች የሕወሃት ተላላክ በመሆን ህዝቡን እርስ በርሱ በማጋጨትና በማፈናቀል የሰሩት ጻያፍ ወንጀል አሁንም እንደቀጠለ ስለሆነ ማስርጃ የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ህዝቡ እነዚህ ድርጅቶች ላይ ጫና በመፍጠር ወደ አገራዊ ድርጅቶች እንዲጠቃለሉ ማስገደድ አለበት። አገራዊ ፖለቲካን ለማጠናከር፣ የአገራዊ ፓርቲዎች መጠናከር ወሳኝ በመሆኑ፣ ይህ ሂደት ከሚቀጥለው ምርጫ በፊት ቢጠናቀቅ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በአጽንኦት መናገር እወዳለሁ።

ከዚህ በፊት ተደጋግሞ የተነገረ ቢሆንም፣ አገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳና በህዝቧ አሰፋፈር ለአገራዊ ፖለቲካ የምትመች መሆኗን አሁንም መናገር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ለአብነት ያህል አንዳንድ እውነታዎችን ቀጥሎ አቀርባለሁ ፦

አንደኛ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመለየት በሚያዳግት ደረጃ አንዱ ከሌላው ጋር የተደባለቀና የተዛነቀ ነው። ባለፉት በርካታ ምእተ ዓመታት በጦርነት፤ በንግድ፤ በውስጣዊ የህዝብ ፍልሰት/እንቅስቃሴ ሰሜኑ ከደቡቡ፣ ምስራቁ ከምእራቡ ጋር በሚገርም ደረጃ ተቀላቅሏል። ለዚህ ትክክለኛው ማሳያ ከያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ውስጥ እንደሚገኝ በቅርበት ማወቅ እንችላለን፤ አንዱ ወይም ሁለቱ፣ ግፋ ሲል ደግሞ አራቱም አያቶቻችን ከተለያዩ ጎሳዎች የሚመዘዙ መሆናቸውን እናስተውላለን። ያም ሆኖ ግን የተወለድንበትን አካባቢ ቋንቋ እየተናገርን ስለምናድግ የዚህ ወይም የዚያ ጎሳ ተብለን እንመደባለን እንጂ ኢትዮጵያውያን በደም፣ በስጋን በአጥንት የተሳአሰርን ህዝብ ለመሆናችን ነጋሪ አያስፈልገንም። አሁን እንኳን ባለው የባንቱስታን አስተዳድር ውስጥ በኦሮሚያ ॥ ሚልዮን አማራ ይኖራል ተብሎ ይነገራል፤ እንዲሁም በአማራ ክልል ውስጥ ደግሞ በአንድ ዞን የሚተዳደር የኦሮሞ ህዝብ አለ። በርካታ የደቡብ ህዝብ በተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች ተበትኖ ይኖራል። የጎሳ ብሄርተኞች የቱን ህዝብ ከማን ሊነጥሉ እንድሚደክሙ በፍጹም መረዳት ያዳግታል።

ሁለተኛ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በስጋ ዝምድና ብቻ ሳይሆን በብዙ ሌሎች ክሮች የተሳሰረ ነው - በታሪኩ፣ በወጉ፣በብሂሉ፣ በሃይማኖቱ ወዘተ...ጀግኖች አያቶቻችን ከየማእዘኑ የመጣባቸውን ጠላት አሸንፈው ትልቅ አገር አቆይተውናል፣ ይህም በበኩሉ ጥቂቶች ባያስተውሉትም አኩሪ የሆነ የጋራ ታሪክ እንዲኖረን ረድቷል። በባህላችንም ውስጥ ብዙ ተወራራሽ የሆኑ ነገሮች እንዳሉ መገንዘብ አያዳግትም፤ አመጋገብ፣ ሰላምታ አሰጣጥ፣ በውልደት፣ በህልፈት፣ በሀዘን በደስታ ብዙ እንገናኛለን። ቋንቋችንም ቢሆን አንዱ በሌላው ውስጥ ይነበባል፤ ለምሳሌ የደቡብ ቋንቋዎች በአማርኛ ወስጥ፤ አማርኛ በኦሮምኛ ውስጥ፤ ትግሪኛ በአማርኛ ወስጥ ይስተዋላሉ። ኢትዮጵያ የሶስቱም ትልልቅ የዓለም ሃይማኖቶች ቤት ሆና ቆይታለች፤ የእስልምናና የክርስትና ሃይማኖቶች በሁሉም ጎሳዎች ውስጥ ተሰራጭተው የቆዩ በመሆናቸው በህዝቡ ዘንድ ለሚታየው መልካም ግንኙነት ጥሩ መሰረት ጥለዋል ማለት ያስደፍራል። በአፍሪካ ውስጥ፣ ህዝብ በሃይማኖት ጉዳይ ከማይጋጭባቸው አግሮች አንዷ ኢትዮጵያ በመሆኗ በህዝቧ መካከል ቢገፉ የማይነቃነቅ ጠንካራ ትስስር እንዳለ ትልቅ ማሳያ ነው።

ሶስተኛ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ የብዙ ቋንቋዎች ባለቤት ነው፤ ይህ ደግሞ እንደ ችግር የምናየው ሳይሆን ልናጌጥበት የሚገባ ደማቅ ህብረቀለም ያለው የአገራችን ገጸ ባህሪ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ታዲያ የጎሳ ልሂቃን በህዝቡ መካከል ያለውን ታሪካዊ ትስስር በመዘንጋት፣ የቋንቋ ልዩነቶችን ብቻ ነጥሎ በማጦዝ በህዝብ መካከል አለመተማመን እንዲሰፍን ምክንያት ሆነዋል። ለዚህም ነው በጎሳ ስም የተቋቋሙ ድርጅቶች ያንን ህዝብ አይወክሉም የሚባለው፤ ምክንያቱም ህዝብ

አልመረጣቸውም፣ የሚደግፋቸው ወይም የሚቃወማቸው ለመሆኑ የሚያሳይ መመዘኛ እስካሁን የለም፡፡ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የተጓዘና 4 የአገር ውስጥና 3 የውጭ አገር ቋንቋዎች የሚናገር ነው። በየትኛውም ማእዘን የሚኖር የአገራችን ህዝብ ባህሉንና ቋንቋውን ከማስከበር አልፎ፣ የጎሳ ልሂቃን የሚያነሷቸውን ጥራዝ ነጠቅ ጥያቄዎች ሲያነሳ አይሰማም። ቀርቦ ላዋየው የህዝቡ ቀዳሚ ጥያቄ ከድህነት ነጻ መውጣት ነው - ይህም ማለት አስተማማኝ የገቢ ምንጭ፤ ለልጆቹ ት/ቤት፣ ህክምና፣ መንገድ፣ ንጹህ ዉሃ፣ መብራት፣ መልካም የፍትህና የአስትዳደር ስርዓት ማለት ነው። የአገራችን ህዝብ የሚፈልገው ከጎረቤቱ ጋር በፍቅርና በሰላም መኖር ነው፤ ወጥቶ ወርዶ፣ እንደልቡ በአገሩ ተዘዋውሮ፣ ነግዶ፣ ሃብት አፍርቶ መኖር ነው። አንዱ የሌላውን ቋንቋ ለምዶ፣ ተጋብቶ ተዛምዶ የሚኖር ህዝብ በመሆኑ ለአገራዊ የፖለቲካ አደረጃጀት የሚመች መሆኑን ተገንዝበን፣ በዚሁ አቅጣጫ ህዝቡን ማዘጋጀት የፖለቲከኞች ዋነኛ ተግባር እንድሆነ ላሳስብ እወዳለሁ፡፡